የኢ.ፌ.ዲ.ሪ የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት
HOUSE OF PEOPLES REPRESENTATIVES OF THE FDRE

# ፓርላማ ዜና መጽሔት

6ኛው የኢፌዲሪ የህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት በ3ኛ አመት የስራ ዘመኑ በሚያዚያ ወር 2016 ዓ.ም ባካሄዳቸው መደበኛ ስብሰባዎች የኢፌዲሪ ሴቶችና ማሕበራዊ ጉዳዮችሚኒስቴርን፣ የኢፌዲሪ የባህልና ስፖርት ሚኒስቴርን፣ የኢፌዲሪ መስኖና ቆላማ አካባቢ ሚኒስቴርን፣ የኢፌዲሪ ገቢዎች ሚኒስቴርን እና የኢኖቬሽን ሚኒስቴርን የ2016 በጀት ዓመት የ9 ወራት ዕቅድ አፈጻጸም የገመገመ ሲሆን በምክር ቤቱ የህዝብ ውክልና ሥራ ደግሞ በመንገድ መሰረተ ልማት ዙሪያ ከህዝብ በተነሱ ጥያቄዎች ላይ ውይይት አካሂዷል፡፡

በተጨማሪም ምክር ቤቱ በዚህ ወር የኢኮኖሚ ዞን ረቂቅ አዋጅንና የበይነ መንግስታዊ የልማት ባለስልጣን ማቋቋሚያ ስምምነት ረቂቅ አዋጅን መርምሮ ያጸደቀ ሲሆን የኢትዮጵያ ሰብአዊ መብቶች ኮሚሽን የሴቶችና ህፃናት ኮሚሽነርን እና የኢትዮጵያ ሕዝብ ዕንባ ጠባቂ ተቋም ዕጩ ምክትል ዋና ዕንባ ጠባቂና ዕንባ ጠባቂዎችን ለመሾም የተቋቋሙት ዕጩ አቅራቢ ኮሚቴዎች ያከናወኗቸውን ተግባራት የተመለከተ ሪፖርት አቅርቧል፡፡

የሚያዚያ ወር ዜና መጽሔታችን እነዚህንና ሌሎች አበይት ምክር ቤታዊ ጉዳዮች ታስነብባለች፡፡

ዐበይት ርዕሶች፡-

- ሕግ አወጣጥ
- ክትትልና ቁጥጥር
- የውክልና ስራ
- ሹመት

መልካም ንባብ!

ሚያዚያ 2016 ዓ.ም

# ፲. ሕግ አወጣጥ

የኢኮኖሚ ዞን  ረቂቅ አዋጅ የኢኮኖሚውን አለም አቀፍ ተወዳዳሪነት ከፍ ለማድርግ ከፍተኛ ጠቀሜታ እንዳለው ተገለጸ፤

ይህ የተባለው ፮ኛው የኢፌዲሪ የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ሚያዚያ 10 ቀን 2016 ዓ.ም ባካሄደው 2፲ኛ መደበኛ ስብሰባው የልዩ ኢኮኖሚ ዞን ረቂቅ አዋጅን መርምሮ ባጸደቀበት ወቅት ነው።

የልዩ ኢኮኖሚ ዞን ረቂቅ አዋጅ የውጭ ኢንቨስትመንትን በቀላሉ ለመሳብ፣ ሰፊ የስራ ዕድል ለመፍጠር እና የአምራች ዘርፍን ለማበረታታት ፋይዳው ከፍተኛ መሆኑን በምክር ቤቱ የኢንዱስትሪና ማዕድን ጉዳዮች ቋሚ ኮሚቴ ሰብሳቢ የተከበሩ አማረች ባካሎ (ዶ/ር) አብራርተዋል።



የተከበሩ አቶ ታገሰ ጫፎ ጉባኤውን ሲመሩ



የተከበሩ አማረች ባካሎ (ዶ/ር) ማብራሪያ ሲሰጡ፣

አያይዘውም ረቂቅ አዋጁ ትስስርን ለማጠናከር፣ የውጭ ምንዛሪ ገቢን ለማሳደግ፣ የቴክኖሎጂ ሽግግር ትልምን ለማሳለጥ፣ ተግባራዊ የተደረገውን የኢንዱስትሪ ፓርኮች ስርዓት ዲዛይንና ትግበራ ወደ ልዩ ኢኮኖሚ ዞን ስርዓት በማሳደግ የኢኮኖሚውን አለም አቀፍ ተወዳዳሪነት ከፍ ለማድርግ ከፍተኛ ጠቀሜታ አለው ብለዋል።

በመጨረሻም ምክር ቤቱም በረቂቅ አዋጁ ላይ ውይይት ካደረገ በኋላ ረቂቅ አዋጁን አዋጅ ቁጥር 1322/2016 አድርጎ በሙሉ ድምፅ አጽድቆታል ።

**በዚሁ ዕለት ምክር ቤቱ የበይነ መንግስታዊ የልማት ባለስልጣን ማቋቋሚያ ስምምነት ረቂቅ አዋጅን መርምሮ አጽድቋል፤**



የተከበሩ ፈቲህ ማህዲ (ዶ/ር) የውሳኔ ሐሳብ ሲያቀርቡ፣



ምክር ቤቱ ረቂቅ አዋጁን ሲያጸድቅ፣

አዋጁ ከምስራቅ አፍሪካ አባል ሀገራት ጋር የበለጠ አብሮ የመስራትና የመተባበር፣ የልማትና የትብብር መስኮችን የሚያስፋ የአሰራርና የመዋቅር ለውጦችን በማድረግ ለሁሉም አባል አገራት የመሪነት የውክልና ሂደትን በመስጠት በባለቤትነት መንፈስ አብረው እንዲሰሩ ከማድረግም ባሻገር በጋራ ጉዳያቸው ላይ በጋራ መወሰን እንዲችሉ ሲሉ የውጭ ግንኙነትና የሰላም ጉዳዮች የቋሚ ኮሚቴው ምክትል ሰብሳቢ የተከበሩ ፈቲህ ማህዲ (ዶ/ር) አስረድተዋል።

አክለውም በቀጠናው ጠንካራ የሆነ ድርጅት በመፍጠር ቀጠናዊ መረጋጋትንና ዘላቂ ልማትን በማስጠበቅ ክልላዊ የኢኮኖሚ ማህበረሰብ ለመገንባት ያለው ፋይዳ ከፍተኛ መሆኑን ገልጸው የኢትዮጵያ ብሄራዊ ጥቅምንም የሚያስጠበቅ በመሆኑ የበለጠ የትብብር ማዕቀፍ የሚሰጥ ነው ብለዋል።

በመጨረሻም ምክር ቤቱ በረቂቅ አዋጁ ላይ ከተወያየ በኋላ ረቂቅ አዋጁን አዋጅ 1323/2016 አድርጎ በሙሉ ድምጽ አጽድቆታል።

## 2.ክትትልና ቁጥጥር

ጾታዊ ጥቃት እና ስለሚወሰድ እርምጃ፣ ስለህገ ወጥ የሰዎች ዝውውር፣ ስለ ጎዳና ተዳዳሪ ዜጎች፣ ስለ ወጣቶች ስብዕና ግንባታ፣ የኦቲዝም ማዕከላትን ስለማስፋፋት እና ተያያዥ ጉዳዮች ዙሪያ በምክር ቤቱ የጤና፣ ማህበራዊ ልማት፣ ባህልና ስፖርት ጉዳዮች ቋሚ ኮሚቴ እንዲሁም ከህዝብ የተሰበሰቡ እና በምክር ቤቱ ለተነሱላቸው ጥያቄዎች ምላሽና ማብራሪያ ሰጥተዋል።

የሴቶችና ማህበራዊ ጉዳይ ሚኒስቴር ሚኒስትር ኤርጎጌ ተስፋዬ (ዶ/ር) ከሁሉም የሀገሪቱ ክፍል የተውጣጡ ከ 24 ሚሊዮን በላይ ወጣቶች በተለያዩ የሀገሪቱ አካባቢዎች በመሰማራት በሰጡት የበጎ ፍቃድ አገልግሎት 18 ቢሊየን ብር የሚገመት ሀብት ማዳን

መቻሉን አስረድተዋል።



ምክር ቤቱ ሪፖርት ሲያዳምጥ፣

በህገ ወጥ መንገድ ከሀገር ሊወጡ ሲሞክሩ በተለያዩ ኬላዎች የተያዙ 887 ዜጎችን የስነ ልቦናዊና ማህበራዊ ድጋፍ ተደርጓል ያሉት ሚኒስትሯ በ9ወሩ ዕቅድ አፈጻጸም 58 ሽ በላይ የሆኑ መደበኛ ባልሆነ ፍልሰት ወደ ተለያዩ ቦታዎች ሄደው የነበሩ ዜችን በመመለስ የስነ ልቦናና ማህበራዊ አገልግሎት ተሰጥቷል ብለዋል።

ሚንስቴር መስሪያ ቤቱ የሚሰራው አብዛኛውን ማህበረሰብ የሚወክሉ የህብረተሰብ ክፍሎች ላይ የሚሰራ በመሆኑ በዘርፉ ያሉ ችግሮችን ለመፍታት የሚያስችለውን "የማህበራዊ ሀላፊነት መወጣት አዋጅ"ን ምክር ቤቱ አጽድቆላቸው ወደስራ እንዲገቡ ጠይቀዋል።

የጤና፣ ማህበራዊ ልማት፣ ባህልና ስፖርት ጉዳዮች ቋሚ ኮሚቴ ሰብሳቢ የተከበሩ ወ/ሮ ወርቀሰሙ ማሞ የተቋሙን እቅድ አፈጻጸም በተመለከተ በሰጡት ግብረ መልስ በየክልሉ በመሄድ ያከናወናቸው የግንዛቤ ማስጨበጫና የንቅናቄ ስራዎች እንዲሁም የወጣቶች የበጎ ፈቃድ ስራዎች አበረታች እና አብሮነትን የሚያጠናክሩ ናቸው ብለዋል።



የተከበሩ ወ/ሮ ወርቀሰሙ ማሞ ግብረመልስ ሲሰጡ.



ክብርት ሚኒስትር ኤርጎጌ ተስፋዬ (ዶ/ር) ሪፖርት ሲያቀርቡ፣

አያይዘውም ከተለያዩ የአገሪቷ ክፍሎች ወደ አዲስ አበባ የሚፈልሱ ዜጎች ለጎዳና ተዳዳሪነት እየተጋለጡ በመሆኑ ችግሩን ከምንጩ በዘላቂነት ለመቅረፍ ሚንስቴር መስሪያ ቤቱ ከተለያዩ ሴክተሮች ጋር በማቀናጀት ትኩረት ሰጥቶ መስራት ይገባል ሲሉ አስረድተዋል።

ጎጂ ልማዳዊ ድርጊቶችን ለመከላከልና ለማስወገድ በየደረጃው የተቀናጀ፣ወጥና ተከታታይነት ባለው መልኩ መሰረታዊ ለውጥ እንዲመጣ መስራት፣ የሴቶች የልማት ህብረት አደረጃጀት እስከ ቀበሌ ድረስ ወጥነት ባለው መንገድ የመፈጸም፣ የኢትዮጵያ የአካል ጉዳተኞች ህግ አጸድቆ ወደ ስራ የማስገባት፣ የወጣት ስብዕና መገንቢያ ማዕከላን ተደራሽ የማድረግ ስራ፣ ውሎ እና አዳራቸውን ጎዳና ያደረጉ ዜጎችን የማንሳትና ከቤተሰብ ጋር የማቀላቀል ስራዎች፣ ሴቶችን ወደ አመራርነት ማብቃት እንዲሁም የአረጋዊያን ማእከልን ማጠናከር በቀጣይ ትኩረት ሊሰጣቸው የሚገቡ ጉዳዮች ናቸው ሲሉ የተከበሩ ወ/ሮ ወርቀሰሙ አሳስበዋል።

**በዚሁ ዕለት ምክር ቤቱ የኢፌዲሪ የባህልና ስፖርት ሚኒስቴርን የ9 ወራት ዕቅድ አፈጻጸም ሪፖርት ገምግሟል።**

*የተቋሙን ሪፖርት ያቀረቡት የባህልና ስፖርት ሚኒስቴር ሚኒስትር ክቡር አቶ ቀጄላ መርዳሳ ሲሆኑ በምክር ቤቱ የጤና፣ ማህበራዊ ልማት፣ ባህልና ስፖርት ጉዳዮች ቋሚ ኮሚቴ እንዲሁም ከምክር ቤት አባላት ለተነሱላቸው ጥያቄዎች ምላሽና ማብራሪያ ሰጥተዋል።*



*ክቡር አቶ ቀጄላ መርዳሳ ሪፖርት ሲያቀርቡ፣*

*የጤና፣ ማህበራዊ ልማት፣ ባህልና ስፖርት ጉዳዮች ቋሚ ኮሚቴ ሰብሳቢ የተከበሩ ወ/ሮ ወርቀሰሙ ማሞ የሚኒስቴር መስሪያ ቤቱ የዘጠኝ ወራት የስራ ክንውን ዝቅተኛ በመሆኑ ከተጠሪ ተቋማት ጋር ያለው ቅንጅታዊ አሰራር በማጠናከር የችግሮቹን መንስኤ በመለየት መፍትሄ ሰጭ መሆን እንዳለበት ጠቁመዋል መስሪያ ቤቱ የተሰጠውን ተልዕኮ ዕውን ለማድረግ ለሀገር እና ለትውልድ ግንባታ ትኩረት ሰጥቶ መስራት አለበት ብለዋል።*

*የሀገር በቀል ዕውቀቶችን እንዲሁም የንባብ ባህልን በማዳበር በትውልድ ቀረፃ እና ግንባታ ረገድ ሚኒስቴር መስሪያ ቤቱ ትኩረት ሰጥቶ መስራት እንዳለበትም አስገንዝበዋል።*

*ዕደ-ጥበብ፣ ስነ-ጥበብና ኪነ-ጥበብ ስራዎች አንጻር የአገር ውስጥና የውጭ ገበያን በማፈላለግ ረገድ የተጀመሩ ስራዎች ተጠናክረው መቀጠል አለባቸው ያሉት የተከበሩ ወ/ሮ ወርቀሰሙ ባህላዊ ሽምግልና ስራዎችን በመቀመር ከአንዱ ለሌላው ተሞክሮ ማስተላላፍ ይገባል ብለዋል።*

*በሁሉም ዘርፍ ተተኪ እስፖርተኞችን ከማፍራት አንጻር በትብብር ከትምህርት ቤቶች፣ ከማህበራት እንዲሁም ከሌሎች አደረጃጀቶች ጋር በጋራ በመስራት ተቋሙ የተሰጠውን ተልዕኮ በመፈጸም ለአገር ማበርከት የሚገባውን ሚና መወጣት አለበት ብለዋል።*

## *ተቋሙ በመንግስት በልዩ ሁኔታ ታይቶ ችግሩ ሊፈታ ይገባል፤*

*ይህ የተባለው የኢፌዲሪ ህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ሚያዚያ 22 ቀን 2016 ዓ.ም ባካሄደው 23ኛ መደበኛ ስብሰባ የኢፌዲሪ መስኖና ቆላማ አካባቢ ሚኒስቴርን የ9ወራት ዕቅድ አፈጻጸም በገመገመበት ወቅት ነው።*

*የተቋሙን ሪፖርት ያቀረቡት የተቋሙ ሚኒስትር ኢንጂነር አይሻ መሐመድ ሲሆኑ በምክር ቤቱ የውሃ፣ መስኖና*

ቆላማ አካባቢ ጉዳዮች ቋሚ ኮሚቴ፣ ከምክር ቤቱ አባላትና ከህዝብ ለተነሱላቸው ጥያቄዎች ምላሽና ማብራሪያ ተሰጥቷል፡፡



ክብርት ሚኒስትር ኢንጂነር አይሻ መሐመድ ለምክር ቤቱ ምላሽና ማብራሪያ ሲሰጡ፣

የውሃ፣ መስኖና ቆላማ አካባቢ ጉዳዮች ቋሚ ኮሚቴ ሰብሳቢ የተከበሩ ወ/ሮ ፈቲሃ ዩሱፍ በበኩላቸው ከምስራቅ አፍሪካ ጋር በጋራ በአይነቱ ልዩ የሆነ የአርብቶ አደሮች ኤክስፖ መከበሩ የሚበረታታ ተግባር መሆኑን ገልጸው የመስኖ መሰረዊ ልማትን ችግር ለመፍታት 6 ቅርንጫፍ ጽ/ቤችን መክፈት መቻሉ ተቋሙ በጥንካሬ የፈጸማቸውና ማስቀጠል ያለባቸው ተግባራት ናቸው ብለዋል፡፡

ተቋሙ ከማህበራዊ ዘርፎች አንጻር የአርብቶ አደሩን ችግር የሚፈታ ተጫባጭ ስራ ከመስራት አንጻር የሚታዩ ጉድለቶችን ማረም እንዳለበት አስገንዝበው የጥናትና ዲይን ስራ የጊዜ ሰሌዳ ተቀምጦላቸው ባለመሰራታቸው በስፋት የሚስተዋለውን የህዝብ ሃብት ብክነት እንዲሁም የህዝብ የልማት ጥያቄን ምላሽ አለመስጠት ጉዳይ ትኩረት ሰጥቶ መስራ ይገባል ሲሉ አሳስበዋል፡፡



የተከበሩ ወ/ሮ ፈቲሃ ዩሱፍ ግብረ መልስ ሲሰጡ፣

አያይዘውም የሚኒስቴር መስሪያ ቤቱ የበጀት አጠቃቀም ዝቅተኛ በመሆኑ ለከፍተኛ ሙስና የሚያጋለጥ በመሆኑ ተቋሙ ራሱን መፈተሽ እንዳለበት አሰገንዝበው ተቋሙ በመንግስት በልዩ ሁኔታ ታይቶ ችግሩ ሊፈታ ይገባል ሲሉ በሰጡት ግብረ-መልስ አሳስበዋል፡፡

## ምክር ቤቱ ሚያዚያ 24 ቀን 2016 ዓ.ም ባካሄደው 24ኛ መደበኛ ስብሰባ የኢፌዲሪ ገቢዎች ሚኒስቴርን የ9 ወራት ዕቅድ አፈጻጸም ገምግሟል፡፡

የኢፌዲሪ ገቢዎች ሚኒስቴርን የ9 ወራት ዕቅድ አፈጻጸም ሪፖርት ክብርት ሚኒስትር ወ/ሮ አይናለም ንጉሴ አቅርበዋል፡፡
የታክስና ጉምሩክ ህግ ተገዥነት ከማረጋገት አንጻር፣ የኮንትሮባንድ ንግድ፣ የታክስ ማጭበርበርን ከመከላከል እንዲሁም ድርጊቱ ተፈጽሞ ሲገኝ ስለተወሰደ እርምጃ፣ ህገ-ወጥ የጫት

ንግድ፣ የቀረጥ ነጻ አገልግሎት፣ ተጨማሪ እሴት ታክስ አተገባበር፣ አንጻር ከተለያዩ ተቋማት ጋር ያለው ቅንጅታዊ አሰራር፣ የተገልጋይ እርካታ እና ተቋሙን ዲጂታላይዝ ከማድረግ አንጻር እየተሰሩ ያሉ ስራዎች፣ ከክልሎች የሚገኘውን ገቢ ማሳደግ፣ ህጋዊ ባልሆነ መንገድና ያለ ደረሰኝ ገንዘብ መሰብሰብ እና ተያያዥ ጥያቄዎች በህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት የፕላን፣ በጀት እና ፋይናንስ ጉዳዮች ቋሚ ኮሚቴ፣ ከምክር ቤቱ አባላት እንዲሁም ከህዝብ ለተሰበሰቡ ጥያቄዎች ምላሽና ማብራሪያ ሰጥተዋል።



ክብርት ወ/ሮ አይናለም ንጉሴም ለምክር ቤቱ ምላሽና ማብራሪያ ሲሰጡ፣

የገቢዎች ሚንስቴር ሚንስትር ክብርት ወ/ሮ አይናለም ንጉሴም በበኩላቸው የታክስ ተገዥነትን ከማረጋገጥ አኳያ እየተሻሻለ እንዲሄድ የአቅም ግንባታ ስልጠናዎችን በማጠናከር የታክስ ከፋዩን መረጃ በቴክኖሎጂ በመደገፍ የታክስ ማጭበርብርን ሊታደጉ የሚችሉ ቴክኖሎጂዎችን ላይ አተኩሮ መስራት እንደተጠበቀ ሆኖ ድርጊቱን በፈጸሙ አካላት ላይ ደግሞ በወንጀልም ይሁን በፍትሐ ብሔር ተጠያቂነት የማድረግ ስራ ይሰራል ብለዋል።

ሚኒስቴር መስሪያ ቤቱ ጫት እንደማንኛውም የኮንትሮባንድ ቁስ በህገ ወጥ መንገድ ከተገኘ የሚያዝ እንደሆነ ጠቁመው ችግሩን ለመከላከል የተቋማት ቅንጅት እንዳለ ሆኖ ኮንትሮባንድን ለመከላከልና የዘርፉን የንግድ ለማቀላጠፍ እየተሰራ እንደሆነ አብራርተዋል።

የታክስ አስተዳደሩን ለማዘመን ቴክኖሎጂን በራስ አቅም በማልማት እየተተገበሩ ያሉ ቴክኖሎጂዎች እንዳሉ ሆኖ የአይታስ የኤሌክትሮኒክስ፣ ኢንቮይስኢንግ፣ የዳታ ዌራውስና ቢዝነስ ኢንተለጀንስ በኢንሳ በኩል እየለማ ነው ያሉት ሚኒስትሯ በቀጣይ ወደስራ የሚገባ ይሆናልም ብለዋል።

የጉምሩክ ኮሚሽን ኮሚሽነሩ አቶ ደበሌ ቀበታ በበኩላቸው የወጪም ይሁን ገቢ የኮንትሮባንድ እንዳለ ጠቁመው ኮሚሽኑ በየጊዜው እያደገ በመጣው የመከላከል አቅም ብሎም ከሁሉም ባለድርሻ አካላት ጋር በተደረገ ቅንጅት 87.8 ቢሊዮን ብር የሃገር ሃብት ለማዳን ተችሏል ብዋል።

አያይዘውም ከሶማሌ እና ከኦሮሚያ ክልል አመራሮች እንዲሁም የጸጥታ መዋቅሮች ጋር በቅንጅት በተሰራው ስራ ከፍተኛ ለውጥ መምጣቱን ጠቁመው በቀጣይም ከሌሎች ክልሎች ብሎም ከሌሎች ባለድሻ አካላት ጋር ጋር በቅንጅት የምንሰራ ይሆናል ብለዋል።

በህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት የፕላን፣ በጀት እና ፋይናንስ ጉዳዮች ቋሚ ኮሚቴ

*ቀጣይ ስብሳቢ የተከበሩ አቶ ደሳለኝ ወዳጄ የታክስ ቀረጥና የህግ ተገዥነት ለማረጋገጥ እየተሰራ ከላው ስራ አንጻር የማስተማር፣ የድንገተኛ ፍተሻና የንግድ ማጭበርበርን በመከታተል መንግስት ሊያጣው የነበረውን 88.85 ቢሊዮን ብር ወደ ገቢ መቀየር መቻሉ አበረታች መሆኑን ገልጸዋል።*

*‹‹ግብር ለሃገር ክብር›› በሚለው ንቅናቂ ምስጉን ግብር ከፋዮችን እውቅና በመስጠት የታክስና የቀረጥ ህግ ተገዥነትን ለማረጋገጥ እየተሰራ ያለው ስራ ጥሩ አበረታች ነው ብለዋል።*

*ገቢዎች ሚኒስቴርም ይሁን ጉሙሩክ ኮሚሽን የጀመሯቸውን የዲጂታይዜሽን ስራዎች በማሻሻል ፋይዳ የዲጂታል መታወቂያ ጋር ከግብር ከፋዩ መለያ ቁጥር ጋር በማገናኘት ተግባራዊ በማድረግ ወደ አንድ ቢሊዮን ዶላር ማዳን መቻሉ አበረታች ነው ሲሉ ገልጸው የኮንትሮባንድ ንግድን ለመቆጣጠር እየተሰሩ ባሉ ስራዎች በተለይ ከሶማሌ ክልል ጋር የጀመሯቸው ቅንጅታዊ ስራዎች ተጠናክሮ መቀጠል ያለበት ነው ያሉት።*

*ይሁን እንጂ የታክስ ማጭበርበር፣መደበቅ እና ሀሰተኛ ደረሰኝን የመቆጣጠር ስራዎች በትኩረት ሊሰራባቸው ይገባል ያሉት* ***የተከበሩ አቶ ደሳለኝ የፌዴራል ዋና ኦዲተር የሚያቀርባቸውን የኦዲት ግኝቶች ተከታትሎ ማስተካከል ላይ ተጨማሪ ስራዎች መሰራት አለባቸው ብለዋል።***

***ምክር ቤቱ ሚያዚያ 29 ቀን 2016 ዓ.ም ባካሄደው 25ኛ መደበኛ ስብሰባ የኢፌዲሪ ኢኖቬሽን እና ቴክኖሎጂ ሚኒስቴርን የ2016 በጀት ዓመት የ9ወራት እቅድ አፈጻጸም ሪፖርት ገምሟል።***



*ምክር ቤቱ ሪፖርቱን ሲያዳምጥ፣*

*ለምክር ቤቱ ሪፖርቱን ያቀረቡት የኢኖቬሽንና ቴክኖሎጂ ሚኒስቴር ሚኒስትር ክቡር በለጠ ሞላ(ዶ/ር) የኢኖቬሽን የስራ ምህዳርን በማስፋት ተጠቃሚነትን ማሳደግ፣ የዲጂታል ኢኮኖሚ ልማትን የማፋጠን፣ የኢንፎርሜሽን ኮሙኒኬሽን ቴክኖሎጂን እና የኢኖቬሽንና ቴክኖሎጂ የአሰራር ሥርዓት በመዘርጋት ምቹ ምህዳር የመፍጠር ስራ ሲሰራ መቆየቱን አውስተው ሀገራዊ የኢኖቬሽን፣ የቴክኖሎጂና የዲጂታላይዜሽን ስራዎችን ለመምራት የሚያችሉ የአሰራር ሥርዓቶችን በመዘርጋት የልማት ፕሮግራሞችን በቴክኖሎጂ በመደገፍ ምርትና ምርታማነትን ለማሳደግ የሚያስችሉ ቴክኖሎጂዎችን የማልማት ስራ መሰራቱን አብራርተዋል።*



ክቡር በለጠ ሞላ (ዶ/ር) ሪፖርቱን ሲያቀርቡ፣

አያይዘውም የዲጂታል ኢኮኖሚ ልማትን ለማፋጠን የሚያስችሉ ሀገራዊ የኤሌክትሮኒክስ ንግድና ግብይት አሰራሮች እንዲስፋፉ አቅም የሚገነቡና ተጠቃሚነትን የሚያሳድጉ ስራዎች ተሰርተዋል ብለዋል።

አክለውም የሳይንስ፣ ቴክኖሎጂና ኢኖቬሽን መሰረተ ልማት አቅሞችን እና ሀብት በመለየት የማፒንግ ስራ ማጠናቀቅ እንደተቻለ ጠቁመው የኢኖቬሽን ስነ-ምህዳርን ለማስፋት በሁሉም ደረጃ የፈጠራ ሃሳብ ያላቸውን ስታርትአፕ ሃሳቦችን አወዳድሮ ድጋፍ በማድረግ በዘርፉ የሚገኘው ኢኮኖሚ ጠቀሜታን እና የስራ ዕድልን የማሳደግ ስራ ትኩረት ተሰጥቶበት ሲሰራ ቆይቷ ቆይቷል ሲሉ ገልጸዋል።

በመንግስትና በንግድ ተቋማት የሚሰጡ አገልግሎቶችን በማሻሻል ቴክኖሎጂን በመጠቀም ወደ ዲጂታል ስርዓት የመግባት ስራ እየተሰራ እንዳለ የጠቆሙት ሚኒስትሩ ሀገራዊ የኢ ኮሜርስ እና ኤሌክትሮኒክስ መንግስት የማስፈጸም አቅም የመገንባት ስራ እንዲሁም ለዲጂታል ኢኮኖሚ ግንባታ የሚረዱ መረጃዎችን ተደራሽ እንዲሆኑ የማድረግ ስራ እየተሰራ ይገኛል ብለዋል።

በምክር ቤቱ የሰው ሀብት ልማትና ቴክኖሎጂ ጉዳዮች ቋሚ ኮሚቴ ሰብሳቢ የተከበሩ ነገሪ ሌንጮ (ዶ/ር) ሚኒስቴር መስሪያ ቤቱ ዜጎችን ተጠቃሚ የሚያደርግና ችግር ፈቺ የምርምር ስራዎችን መስራቱን ጨምሮ የስፔስና ጂስፓሻል መረጃዎችን ለሃገር ልማት እንዲውል ብሎም የኢንፎርሜሽንና ቴክኖሎጂ የአሰራር ስዓትን በመዘርጋትና ምቹ ምህዳር በመፍጠር የተሰሩ ስራዎችን በጥንካሬ አንስተዋል።



የተከበሩ ነገሪ ሌንጮ (ዶ/ር) ግብረ መልስ ሲሰጡ፣

ይሁን እንጂ ዘርፉ ትልቅ አቅም ያለው በመሆኑ የመንግስትን የንግድ ስራ በቴክኖሎጂ ከመደገፍም ባሻገር የዲጂታል ኢኮኖሚ መሠረተ ልማት ከመገንባት አንጻር ጉድለቶች እንዳሉ ጠቁመዋል።

አያይዘውም የተከበሩ ነገሪ ሌንጮ የዲጂታል ኢትዮጵያ 2025 ቴክኖሎጂ መር ፈጣን ዕድገት የማስመዝገብ ስትራቴጂን ውጤታማነት ለማረጋገጥ ከባለ ድርሻ አካላት ጋር በቅንጅት መስራት እንደሚያስፈልግ ጠቁመው ስታርት አፖችን ከማልማት፣ ከመደገፈ እና በክልሎች ማዕከላትን በመክፈት ስራ ፈላጊ ወጣቶች አስፈላጊውን አገልግሎት አግኝት ተጠቃሚ እንዲሆኑ በትኩረት መስራት ያስፈልጋል ብለዋል።

## 3.የውክልና ስራ

**ምክር ቤቱ ሚያዝያ 16 ቀን 2016 ዓ.ም በመንገድ መሰረተ ልማት ዙሪያ ከህዝብ በተነሱ ጥያቄዎች ላይ ውይይት አካሂዷል፡፡**



*ምክር ቤቱ በውይይቱ ወቅት*

በዚሁ ዕለት የምክር ቤቱ አባላት ከከተማ እና መሰረተ ልማት ሚኒስቴር ከፍተኛ የስራ ኃላፊዎች ጋር በሀገሪቱ አጠቃላይ የመንገድ መሰረተ ልማት ላይ ውይይት አድርገዋል፡፡

የኢፌዲሪ ህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት አፈ ጉባኤ የተከበሩ አቶ ታገሰ ጫፎ በውይይቱ ወቅት እንደገለጹት በመንገድ መሰረተ ልማት ሰፊ ስራ መከናወናቸውን ጠቁመው የህዝቡ የመልማት ጥያቄ በየጊዜው እየጨመረ በመሆኑ የኢትዮጵያ መንገዶች አስተዳደርን የስራ ድርሻ ለክልሎች በማጋራትና አቅማቸውን በመገንባት የህዝቡን ጥያቄ መመለስ ተገቢ ነው ብለዋል፡፡



*የተከበሩ አፈ ጉባኤ አቶ ታገሰ ጫፎ፣*

አያይዘውም የተከበሩ አቶ ታገሰ የመንገድ የመሰረተ ልማት ስራዎች በተያዘላቸው በጀትና ጊዜ እንዲጠናቀቁ የሀገሪቱ ሰላምና ጸጥታ መፍትሄ እንዲያገኝ ሁላችንም መስራት አለብን ሲሉ አስገንዝበዋል፡፡

የኢትዮጵያ መንገዶች አስተዳደርም በዘርፉ የሚነሱ በርካታ ጥያቄዎችን ለመመለስ የጸጥታ መደፍረስ ችግር የሌለባቸው አካባቢዎች ላይ የተጀመሩ የመንገድ ፕሮጀክቶችን በተያዘላቸው ጊዜ እንዲጠናቀቁ ተገቢውን ክትትልና ድጋፍ በማድረግ በቁርጠኝነት መስራት እንዳለበት አሳስበዋል፡፡

የተቋሙ የመፈጸም አቅም ተግዳሮቶች ናቸው የተባሉት የተጋነነ የካሳ ክፍያ፣ የወሰንና ድንበር፣ የውጭ ምንዛሬ ችግር፣ የሠላምና ጸጥታ ችግር እንዲሁም ሌሎች ችግሮችን ተቋሙ በራሱ መፍታት የሚጠበቅበትን እየፈታ ዘርፉ የሚመለከታቸው አካላት ደግሞ የየራሳቸውን ድርሻ በመውሰድ ችግሩን በዘላቂነት ለመፍታት በተዘጋጀው የመውጫ እስትራቴጂ መሰረት መስራት ያስፈልጋል ብለዋል፡፡

በህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት የመንግስት ረዳት ተጠሪ ሚንስትር ዴኤታ የተከበሩ ወ/ሮ መሰረት ኃይሌ በበኩላቸው ባለፈው የካቲት ወር በተካሄደ የህዝብ ውክልና ስራ የመንገድ መሰረተ ልማትን በተመለከተ ከተለያዩ የሀገሪቱ ክፍሎች ወደ 400 ያክል ጥያቄዎች መሰብሰባቸውን ጠቁመው ለነዚህ የህዝብ ጥያቄዎች ተገቢ ምላሽ መስጠት ያስፈልጋል ሲሉ አስገንዝበዋል፡፡



የተከበሩ ወ/ሮ መሰረት ኃይሌ

ለመንገድ ስራዎች መጓተት በጥቅል መንስኤ ከማስቀመጥ ይልቅ የእያንዳንዱን ፕሮጀክት አፈፃፀም በመገምገም በዝርዝር መፍትሄ መስጠት ይገባልም ብለዋል፡፡

የከተማ እና መሰረተ ልማት ሚኒስቴር ሚንስትር ክብርት ወ/ሮ ጫልቱ ሳኒ በበኩላቸው አገራዊ ለውጡን ተከትሎ በሀገራችን ያለውን የመንገድ ሽፋን ለማሻሻል በርካታ ስራዎች ተሰርተዋል ብለዋል፡፡



ክብርት ሚኒስትር ወ/ሮ ጫልቱ ሳኒ

አክለውም በተለያዩ የሀገሪቱ አካባቢዎች የተከሰተው የጸጥታ ችግር፣ የተጋነነ የካሳ ጥያቄ፣ በጀት በወቅቱ አለመለቀቅ እንዲሁም ነዳጅን ጨምሮ በውጭ ምንዛሬ ምክንያት የተከሰተው የግንባታ ግብዓቶች የዋጋ ንረት የመንገድ መሰረተ ልማት ስራዎችን በእጅጉ እየተፈታተኑ ስለመሆኑ አስረድተዋል፡፡

በተያዘው የ10 ዓመት የልማት ዕቅድ አዳዲስ የመንገድ ፕሮጀክቶችን እንደማይጀመሩና የተጀመሩትን ፕሮጀክቶች ለማጠናቀቅ ብቻ እንደሚሰራ የሚንስቴር መስሪያ ቤቱ እና የኢትዮጵያ መንገዶች አስተዳደር ከፍተኛ የስራ ኃላፊዎች ለምክር ቤቱ አባላት አስረድተዋል፡፡

በዕለቱ የምክር ቤቱ አባላት በህዝብ ውክልና ስራ ወቅት ከየምርጫ ክልላቸው የመንገድ መሰረተ ልማትን በሚመለከት ለተነሱ ጥያቄዎች ምላሽና ማብራሪያ ተሰጥቶበታል፡፡

## 3.ሹመት

**የኢትዮጵያ ሰብአዊ መብቶች ኮሚሽን የሴቶችና ህፃናት ኮሚሽነርን ለመሾም የተቋቋመው ዕጩ አቅራቢ ኮሚቴ ሁለተኛ መደበኛ ስብሰባዉን አካሂዷል፡፡**



ዕጩ አቅራቢ ኮሚቴው በስብሰባ ወቅት

የኢትዮጵያ ሰብአዊ መብቶች ኮሚሽን የሴቶችና ህፃናት ኮሚሽነርን ለመሾም የተቋቋመው ዕጩ አቅራቢ ኮሚቴ ሚያዚያ 29 ቀን 2016 ዓ.ም ባካሄደዉ ሁለተኛ መደበኛ ስብሰባዉ የዕጩ ምዝግባውን ሂደቱን ሪፖርት አቅርቧል፡፡

የጥቆማ ሂደቱ አሳታፊ ነበር ያለው ዕጩ አቅራቢ ኮሚቴው የኢትዮጵያ ሰብአዊ መብቶች ኮሚሽን የሴቶችና ህፃናት ኮሚሽነር ለመሾም በተሰጠው ጥቆማ 213 ሴት ዕጩዎች መጠቆማቸው ገልጿል፡፡

የዕጩ አቅራቢ ኮሚቴዉ በኢትዮጵያ የሰብአዊ መብት ኮሚሽን ማቋቋሚያ አዋጅ ቁጥር 1224/2012 አንቀፅ 2/5 መሰረት ከተቋቋመ በኋላ የዕጩ አቅራቢ ጽ/ቤት ተቋቁሞ አስፈላጊ የሆኑ ቁሳቁሶች ተሟልቶለት፣ ስራዉ በቅርበት የሚሰራ ባለሙያና ሃላፊ እንዲሁም ፀሀፊ የተመደበለት መሆኑን በሪፖርቱ ገልጿል፡፡

የዕጩ አቅራቢ ኮሚቴዉ በኢትዮጵያ የሰብአዊ መብት ኮሚሽን ማቋቋሚያ አዋጅ ቁጥር 1224/2012 አንቀፅ 2/5 መሰረት ከተቋቋመ በኋላ የዕጩ አቅራቢ ጽ/ቤት ተቋቁሞ አስፈላጊ የሆኑ ቁሳቁሶች ተሟልቶለት፣ ስራዉ በቅርበት የሚሰራ ባለሙያና ሃላፊ እንዲሁም ፀሀፊ የተመደበለት መሆኑን በሪፖርቱ ገልጿል፡፡

በዚህ መሰረት ዕጩዎች ማሟላት ያለባቸውን መስፈርቶች እና የጥቆማ ዘዴዎችን በሚመለከት የተለያዩ ሚዲያ አመራጮችን በመጠቀም በማስታወቂያዎች እንዲነገር የማድረግ እና ተጨማሪ ጋዜጣዊ መግለጫ በመስጠት ለህዝብ ግልጽ ማድረግ መቻሉን ኮሚቴው አስረድቷል፡፡

የዕጩ አባላት ምዝግባ ሂደት የተለያዩ አማራጮችን በመጠቀም ለተከታታይ 15 ቀናት በስልክ፣ በኢ-ሜይል፣ በዋትስአፕ እንዲሁም የመመዝገቢያ ሳጥን በማዘጋጀት አሳታፊ የሆነ የዕጩዎች ምዝገባ መካሄዱን አብራርቷል፡፡

በቀጣይ ዕጩ አቅራቢ ኮሚቴዉ በመስፈርቱ መሰረት ዕጩዎችን የመለየት እና የማጥራት ስራውን በማጠናቀቅ ለሕዝብ ይፋ ማድረግ ይጠበቅበታል ሲሉ የኮሚቴው ሰብሳቢ የተከበሩ አፈ ጉባኤ አቶ ታገሰ ጫፎ አሳስበዋል፡፡

**የኢትዮጵያ ሕዝብ ዕንባ ጠባቂ ተቋም ዕጩ ምክትል ዋና ዕንባ ጠባቂና ዕንባ ጠባቂዎችን ለማሾም የተቋቋመው ዕጩ አቅራቢ ኮሚቴ ሁለተኛ መደበኛ ስብሰባውን አካሂዷል፡፡**



ዕጩ አቅራቢ ኮሚቴው በስብሰባ ላይ፣

ሚያዚያ 30 ቀን 2013 ዓ.ም ሪፖርቱን ያቀረበው ዕጩ አቅራቢ ኮሚቴ ሂደቱ ከፍተኛ የሕዝብ ተሳትፎ የተመዘገበበት መሆኑን አድንቀው 480 ተጠቋሚ ዕጩዎችን መመዝገቡን አሳውቋል፡፡

የተከበሩ አቶ አፈ-ጉባኤ ታገሠ ጫፎም በበኩላቸው የምዝገባ ሂደቱ በመላ ሀገሪቱ ሕዝቡ ያደረገውን ተሳትፎና የባለሙያዎችን በቁርጠኝነት ለመመዝገብ ያደረጉትን ጥረት አድንቀው ዕጩ አቅራቢ ኮሚቴው በሚያስቀምጠው አቅጣጫና በምልመላ መሥፈርቱ መሠረት በፍጥነት መከናወን አለበት ብለዋል፡፡

ለምክትል ዋና ዕንባ ጠባቂ 200፣ ለዘርፍ ዕንባ ጠባቂ 85 እና ለሴቶች፣ ሕፃናት፣ አካል ጉዳተኞችና አረጋዊያን ዕንባ ጠባቂ 195 በድምሩ 480 ተጠቋሚዎች መቅረባቸውን የኮሚቴው ፀሐፊ የተከበሩ አቶ ዕውነቱ አለነ አብራርተዋል፡፡

በመሆኑም በአጭር ጊዜ ውስጥ በዕጩ አቅራቢ ኮሚቴው በዝርዝር ተወያይቶ ባጸደቀው መሠረት ተጠቋሚዎችን በመለየትና በጥንቃቄ በማወዳደር የተሻለ ውጤት ያመጡትን ዕጩዎች ለሕዝብ በይፋ እንደሚገልፅ የተከበሩ አፈ ጉባኤ አቶ ታገሠ ጫፎ አስታውቀዋል፡፡

ለበለጠ መረጃና አስተያየት
አድራሻ (Adress)

ስልክ Tel: 011-154-52-33

ነጻ ስልክ ጥሪ Free call: 8557

ፖስታ ሳጥን ቁጥር P.O.Box: 80001

ኢ-ሜይል. E-mail info@hopr.gov.et

ድረ-ገጽ Website: www.hopr.gov.et

በኢፌዲሪ የህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ጽ/ቤት

በአስተምህሮ፣ ፕሮሞሽንና ኮሙኒኬሽን ዳይሬክቶሬት የተዘጋጀ፣